# የኢትዮጵያውያኖች የመረዳጃ እድር በኔዘርላንድስ

## መተዳደሪያ ደንብ

## ምዕራፍ 1 ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1.1 ስያሜ

1.1.1 ይህ እድር የኢትዮጵያውያኖች የመረዳጃ እድር በኔዘርላንድስ ተብሎ ይጠራል።

### አንቀጽ 1.2 አድራሻና ተልዕኮ

**1.2.1** የእድሩ አድራሻ በአምስተርዳም ከተማ ነው።
**1.2.2** እድሩ በኔዘርላንድስ ሕግ መሰረት የተቋቋመና ለትርፍ የማይሰራ መረዳጃ ማህበር ነው።
**1.2.3** እድሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

### አንቀጽ 1.3 ዓላማ

**1.3.1** የእድር አባል ወይም የእድር አባል ቤተሰብ ማለትም ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅ በሞት ሲለይ ለቀብር ሥነ - ስርዓት ማስፈጸሚያ ወይም ለአስከሬን መላኪያ የሚያግዝ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ፣
**1.3.2** አባል ወይም የአባል ቤተሰብ (ልጅ) በሞት ሲለይ የእድሩ አባላት ለቅሶ እንዲደርሱና እንዲያጽናኑ መረጃ መስጠት፣
**1.3.3** አባላት በሚኖሩበት አካባቢ በሀዘን ጊዜ የመስተንግዶ ሥራ እንዲያግዙና በሚይስፈልገው ሁሉ እዲተባበሩ መንገር፣ ማስተባበር፣
**1.3.4** ለቀብር አፈጻጸም ወይም ለአስከሬን ማጓጓዣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለሟች ቤተሰብ መስጠት፣
**1.3.5** ለወደፊት እድሩ ለአባላት ጥቅም ያስገኛል ብሎ የሚያምንበትን ማንኛውንም ዓላማ ከእድሩ አባላት ጋር በመወያየት እንዳስፈላጊነቱ መጨመር
**1.3.6** የእድር አባል ህመም ባጋጠመው ጊዜ እንደ አባሉ ፍቃድ የእድሩ አባላት እንዲጠይቁት መረጃ መስጠት

### አንቀጽ 1.4 የእድሩ ገቢ

**1.4.1** ከአባልነት ክፍያ

**1.4.2** በስጦታ ከሚገኝ፤

**1.4.3** እድሩ የሚያዘጋጀውን ፕሮግራም ስፖንሰር ከሚያደርጉ ወይም እርዳታ ከሚሰጡ ድርጅቶች የሚገኝ ገቢ ይሆናል።

## ምዕራፍ 2

## አባልነት

### አንቀጽ 2.1 አባል ስለመሆን

**2.1.1** በኔዘርላንድስ ውስጥ ነዋሪ የሆነ፣ ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ እንዲሁም የእድሩን ሕገ ደንብ የተቀበለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የእድሩ አባል መሆን ይችላል።

2.1.2 ማንኛውም የዕድሩ አባል መሆን የሚፈልግ ሰው በአንቀጽ 2.3. እና አንቀጽ 2.4. የተመለከቱትን የአባልነት ምዝገባ ሂደት መፈጸሙ ሲረጋገጥ አባል ይሆናል።

2.1.3 አባል ከኔዘርላንድስ አገር ለቆ በሌላ አገር መኖር ከጀመረ ግዴታውን በማክበር በአባልነት መቀጠል ይችላል።

2.1.4 እስከ ጁን 1 ቀን 2023 ድረስ ተመዝግበው የእድር አባልነት ክፍያን የከፈሉ አባላት የእድሩ መስራች አባላት ይሆናሉ። ከ ጁን 1 ቀን 2023 በኃላ አባል ለመሆን የሚፈልጉ አዲስ አባላት የመመዝገቢያ ክፍያው አንድ መቶ ዩሮ (€100) ይሆናል።

## አንቅጽ 2.2 የአባል መብት፣

2.2.1 አንድ አባል ከተመዘገበ ቀን ጀምሮ የመምረጥ መብት አለው።
2.2.2 አንድ አባል በአባልነት አንድ ዓመት ከሆነው የመመረጥ መብት ይኖረዋል።
2.2.3 አንድ አባል በአባልነት ተመዝግቦ ሙሉ ዓመት (12 ወራት) ካልሞላው የገንዘብ ጥቅም አያገኝም።
2.2.4 አንድ አባል የአባልነት ግዴታውን ከአንድ ዓመት በላይ እያሟላ ከቆየ በኃላ፤ የሞት አደጋ ሲያጋጥም፤ አንድ ሺህ አምስት መቶ ዩሮ (€1,500.00) ያገኛል።
2.2.5 ከ18 ዓመት በታች የሆነ የአባል ልጅ የሞተ እንደሆነ አባል ከሚያገኘው ሃምሳ በመቶ (50%) ያገኛል።
2.2.6 የአባል ልጅ አስራ ስምንት አመት(18) ሲሞላው፤ ወዲያውኑ የዓመቱን ክፍያ በመክፈል እራሱን ችሎ አባል ሊሆን ይችላል፣
2.2.7 እንደሙሉ አባል የተመዘገበበት ዓመት ላይ፡ ከወላጆቹ ጋር ሳለ የሚያገኘውን ጥቅም ያገኛል ፡፡ ዓመቱ ሲያልቅ፡ ሌላው አባል የሚያገኘውን ጥቅም ያግኛል፡፡
2.2.8 ከአንድ በላይ የቤተሰብ አባላት ላይ በአንድ ጊዜ ሞት ቢደርስ፣ የእድሩ ሥራ አስፈጻሚ አባላትንና ሌሎች ኢትዮጵያውያንን የገንዘብ እርዳታ እንዲያደርጉ ይጠይቃል፡፡
2.2.9 ከኔዘርላንድ አገር ውጭ አባል ከሞተ፤ ጉዳዩ እስከሚጣራ፣ እድሩ የተጠቃሚ ገንዘብ ክፍያን የሚከፍለው የሞት ምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ የሞት ማረጋገጫ ሰነድን ተመልክቶ ነው።
2.2.10 የቀብር ዋስትና ያለውም የሌለውም የእድሩ አባል በሞት አደጋ ጊዜ ከእድሩ የሚያገኘው ገንዘብ አንድ ዓይነት ነው ።
2.2.11 በኔዘርላንድ አገር የመኖሪያ ፍቃድ የሌለው የእድሩ አባል የተለየ ጥቅም አያገኝም።
2.2.12 ለሕክምና ወይም ለሌላ ምክንያት፡ እድሩ ቅድመ ክፍያ አያደርግም፡
2.2.13 እድሩ አንድ አባልን በሞት በሚያጣበት ጊዜ ከእድሩ አንድ መቶ ዩሮ (€100) ወጪ በማድረግ አበባ ይገዛል።

### አንቀጽ 2.3 የአባል ግዴታ

2.3.1 ለእድሩ ደንብ ተገዢ መሆን፤

2.3.2 እድሩ የሚጠይቀውን የአባልነት መረጃ በአግባቡና በትክክል የመስጠት፤

2.3.3 የአባልነት ግዴታ መዋጮዎችንና ሌላም በሞት ጊዜ ለሚደረጉ መዋጮዎች በወቅቱ መክፈል፤።

2.3.4 አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠም በስተቀር በጠቅላላ ስበሰባ ላይ መገኘት፤

2.3.5 በአባላት መካከል የመግባባትና የመተባበር ስሜት እንዲዳብር መርዳት፤

2.3.6 አባል ወይም የአባል ቤተሰብ በሞት ከተለየ እያንዳንዱ የእድሩ አባል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር፣ ለቅሶ መድረስና እዚህ የሚቀበር ከሆነ በቀብሩ ላይ መገኘት፣ አስከሬኑ ወደ አገር ቤት ወይም ሌላ ቦታ የሚሄድ ከሆነም መሸኘት፤

2.3.7 አባል ወይም የአባል ቤተሰብ በሞት ከተለየ፣ ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቅ አባል ለእድሩ ተጠሪ የማሳወቅ፤

2.3.8 የአባል ወይም የአባል ቤተሰብ ሁኔታ ከተለወጠ፣ (ለምሳሌ የልጅ እድሜ ከ18 አመት በላይ ከሆነ) ለውጥ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለእድሩ ማሳወቅ፣

2.3.9 በተጨማሪም በቤተሰብ ውስጥ ተጨማሪ አዲስ ልጅ ከተወለደ ወይም ከ18 ዓመት በታች የሆነ የአባል ልጅ (ከኢትዮጵያ ወይም ከሌላ ሥፍራ በማምጣት) ቤተሰቡን ከተቀላቀለ ለእድሩ ተጠሪዎች ማሳወቅ ይኖርበታል ።

## አንቀጽ 2.4 የአባልነት መመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያ

| 2.4.1 የአባነልነት መመዝገቢያ | | አንድ ጊዜ ብቻ | | ዓመታዊ መዋጮ |
|---|---|---|---|---|
| - | ለመስራቾች (እስከ ጁን 1 2023) | €50.00 | + | €5 *12= €60 |
| - | ከጁን 1 ቀን 2023 ዓ.ም በኋላ | €100.00 | + | €5 *12= €60 |

ከላይ የተመከተው የአባልነት መመዝገቢያና ዓመታዊው መዋጮ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በሥራ አመራር ቦርድ በሚቀርብ ጥናት መሠረት በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል።

2.4.2 በንዑስ አንቀጽ 2.4.1 መሠረት እንደ እድሩ መስራች የሚቆጠር አባል የመመዝገቢያና ወርሃዊ መዋጮውን እስከ ጁን 1 ቀን 2023 ድረስ ካልከፈለ እንደማንኛውም አዲስ አባል የመመዝገቢያ መቶ ዩሮ(€100) እና ዓመታዊ መዋጮውን እንዲከፍል ይደረጋል።

2.4.3 በወረረሽኝ በሽታ ወይም በከፍተኛ አደጋ ምክኒያት፡ የተጠቃሚ ክፍያው እድሩ ካለው ገንዘብ በላይ ከሆነ፣ ጠቅላላ ስብሰባ ተጠርቶ፡ ወይም የእድሩ ቦርድ አባላት በወሰኑት የተጠቃሚ ክፍያ ማስተካከል ይደረጋል፡፡

2.4.4 የእድሩ ተቀማጭ ገንዘብ ከአምስት ሺህ ዩሮ (€5000) በታች ከሆነ፤ አባላት ተጨማሪ መዋጮ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ። የመዋጮው መጠን በአባላት ጠቅላል ስብሰባ ይወሰናል። ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ተጨማሪ መዋጮን እንደ ሌላው አባል እኩል ያዋጣሉ።

## ምዕ ራ ፍ 3
## አንቀጽ 3.1 የሥነ ሥርዓት እርምጃ

3.1.1 በአንቀጽ 2.4.1 መሰረት የአባልነት መዋጮ / ክፍያ የሚሰበሰበው አንድ ሰው አባል ከሆነበት ወር ጀምሮ ይሆናል።

3.1.2 ማንኛውም ሰው ዓመታዊ የአባልነት መዋጮውን በአንድ አመት ወይም አሥራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ ካልከፈለ የመቶ ዩሮ (€100) ቅጣት ይጣልበታል። የአባልነት ክፍያውን ላላሟላ አባል ዓመቱ ከማለቁ በፊት በስልክ ወይም በኢሜል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

3.1.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.1.2 መሠረት ዓመታዊ የአባልነት መዋጮውን ያላሟላ አባል በአንቀጽ 2.4.2 እና ሌሎች አንቀጾች መሠረት የሚሰጡ ጥቅሞችን አያገኝም።

3.1.4 አንድ አባል መክፈል የሚገባውን ክፍያ ሳይከፍል የመክፈያው ዓመት ካለፈበት ወር ጀምሮ በሚቆጠር ወራት ውስጥ በንዑስ አንቀጽ 3.1.2. የተጠቀሰውን ቅጣት እና የአባልነት መዋጮን ካለፈ በገዛ ፍቃዱ እድሩን እንደለቀቀ ተቆጥሮ ከአባልነት ይሰናበታል። ከእድሩም ምንም አይነት አገልግሎት አያገኝም።

3.1.5 አንድ አባል ለረጅም ጊዜ ከኔዘርላንድስ አገር ውጭ የሚቆይ ከሆነ፡ ቅድመ ክፍያ ለዓመታት ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.1.6 የአባልነት ግዴታውን ባለመክፈሉ የተሰናበተ አባል ወይም በአንቀጽ 3.1.7 ከተመለከተው ውጪ በሌላ ምክንያት እድሩን የለቀቀ አባል እንደ አዲስ አባል ሊመዘገብ ይችላል። የአባልነት መብቱም እንደ ማንኛውም አዲስ አባል ይሆናል።

3.1.7 አንድ አባል የሐሰት መረጃ ለእድሩ ከሰጠና በዚህም የሃሰት መረጃ ምክንያት ሊሰጠው የማይገባውን ገንዘብም ይሁን ሌላ ጥቅም ለማግኘት ጥረት ሲያደርግ ከተገኘ እና ከተረጋገጠ፣ እድሩ አባልነቱን ሊሰርዝ ይችላል። ያገኘውም ጥቅም ካለ፣

እንዲመልስ እድሩ በህግ ይጠይቀዋል። በዚህ ምክንያት ከእድር አባልነት  የተገለለውን አባል፣ እድሩ ሁለተኛ በአባልነት አይቀበለውም፡፡

3.1.8 አንድ የእድር አባል ከአባልነት ከተገለለ ወይም በራሱ ፈቃድ እድሩን ከለቀቀ፣ አባል በነበረበት ወቅት ለዕድሩ የከፈለው ማንኛውም ገንዘብ  አይመለስለትም።

## አንቀጽ 4  የእድሩ የአመራር አካላት

ዕድሩ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፍጻሚ ቦርድ እና ኦዲተር ይኖረዋል።

## አንቀጽ 4.1 ጠቅላላ ጉባኤ

4.1.1 ጠቅላላ ጉባኤ ማለት የእድሩ አባላት የሚገኙበት ጠቅላላ ስብሰባና የዕድሩ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው።

4.1.2 ጠቅላላ ጉባኤው በዓመት አንድ ጊዜ ጀነዋሪ ላይ በርቀት (በበይነ መረብ፣ ለምሳሌ በዙም) ይካሄዳል። በዚህ ጉባኤ ላይ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርት ይቀርባል።

4.1.3 አባላት እርስ በርስ እንዲገናኙና የበለጠ እንዲተዋወቁ የሚያደርግ  በአመት አንድ ጊዜ  ከበጋ እረፍት መልስ የማህበራዊ ግንኙነት መርሐ ግብር ይካሄዳል።

4.1.4 ከግማሽ በላይ አባላት የተገኙበት ጠቅላላ ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

4.1.5  ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባኤ ካልሞላ፣ ተከታይ ሁለተኛ ስብሰባ ጠርቶ የሚገኙ አባላት ከግማሽ በታች ቢሆኑም። የስብሰባው ምልዓተ ጉባኤ እንደሞላ ይቆጠራል።

4.1.6 ከላይ በአንቀጽ 4.1.4 እና 4.1.5 በተጠቀሰው መሰረት ምልዓተ ጉባኤው  በአንቀጽ 4.1.7 የተጠቀሰውን ሳይጨምር እድሩን በሚመለከት ማንኛውንም ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላል።

4.1.7  እድሩን ለማፍረስ የጠቅላላ ጉባኤው ሁለት ሶስተኛው (2/3) ድምጽ ያስፈልጋል።

4.1.8  እድሩ የፈረሰ እንደሆነ፣ የእድሩ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ ጥሬ ገንዘብ ጭምር ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ የበጎ አድራጎት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች እንዲሰጥ ይደረጋል።

## አንቀጽ 4.2 የጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ሥልጣን

4.2.1  ጠቅላላ ጉባኤው በየሁለት አመቱ የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላትን ይመርጣል።

4.2.2  የእድሩን መተዳደሪያ ደንብ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፣

4.2.3 የእድሩን የሥራ ማስካሄጃ  ወጭ ይፈቅዳል፣

4.2.4  ኦዲተሮችን ይመርጣል፣

4.2.5 የእድሩን ገቢ አሰባሰብ፣ ወጪ አደራረግና ሌሎች የእድሩን የገንዘብ አጠቃቀምና እንቅስቃሴ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ

ውሳኔ ይሰጣል፣

**4.2.6 የቦርዱን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይመረምራል፣ ያጸድቃል፣ እንደአስፈላጊነቱም መመሪያዎችን ይሰጣል።**

## አንቀጽ 4.3
## የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ

**በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጠው የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት**

**4.3.1 የቦርድ አባላት ቁጥር ሰባት ይሆናል፡፡**

**4.3.2 የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። ነገር ግን ምርጫ ማድረግ የማያስችል ያልተጠበቀ ምክንያት ካጋጠመ (አጠቃላይ ስብሰባ መጥራት የማያስችል ሁኔታ ቢፈጠር) የአባላቱ የሥራ ዘመን ለሁለት የሥራ ዘመን ሊራዘም ይችላል፡፡**

**4.3.3 በሁለት የሥራ ዘመናት በተከታታይ ያገለገለ የቦርድ አባል በድጋሚ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የሥራ ዘመን ሳይመረጥ መቆየት ይኖርበታል።**

**4.3.4 የቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።**

**4.3.5 በማናቸውም የቦርድ ምርጫ ጊዜ ከአባላቱ ከሚቀርቡት ውስጥ የስራ ዘመናቸውን የጨረሱ የቦርድ አባላት ቁጥር ከሃምሳ በመቶ (50%) በመቶ ወይም ከግማሽ ሊበልጥ አይችልም።**

**4.3.6 አንድ የቦርዱ አባል የሥራ ዘመኑን ሳይጨርስ አገልግሎቱን በማናቸውም ምክንያት ቢያቋርጥ ለቀሪው የሥራ ዘመን ተክቶ የሚያገለግል አባል ቦርዱ ከአባላት መሃል ይሰይማል፣ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል።**

## አንቀጽ 4.4 የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ኃላፊነት

**የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፣አንድ ሊቀመንበር፣ አንድ ምክትል ሊቀመንበር፣ አንድ ፀሃፊ፣ አንድ ኢቃቤ ንዋይ ( ገንዘብ ያዥ)፣ አንድ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ፣ አንድ የሂሳብ ባለሙያ (አካውንታንት) እና አንድ የንዑሳን ኮሚቴ አስተባባሪ ያሉበት ባለ ሰባት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ ይህ ኮሚቴም የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል።**

**4.4.1 የእድሩን የእለተ ከእለት ተግባር የሚያከናውን አንድ ሊቀመንበር፣ አንድ ምክትል ሊቀመንበር፣ አንድ ፀሃፊ፣ አንድ ኢቃቤ ንዋይ (ገንዘብ ያዥ)፣ይመርጣል፡፡**

**4.4.2 ለሥራው ክንውን የሚረዱ የሥራ እቅድ ያዘጋጃል። በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በማጸደቅ በሥራ ላይ ያውላል።**

**4.4.3 የእድሩን ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴ ያቋቁማል፣ የሥራ መመሪያ ያወጣል**

**4.4.4 በወር አንድ ወይም ሁለት ጊዜ እየተገናኘ መደበኛ ስራውን ያከናውናል።**

**4.4.5 ለጠቅላላ ጉባኤው የሥራ ክንውን ዘገባ በዓመት አንድ ጊዜ ያቀርባል።**

**4.4.6 የእድሩን ገቢ ያሰባስባል።**

**4.4.7 በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት እርዳታ ይሰጣል።**

**4.4.8 አስፈላጊውን መረጃ ለአባላት በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል።**

4.4.9 የእድሩን ገንዘብና ንብረት በአግባቡ ይይዛል።

4.4.10 የእድሩ አሠራር የሚሻሻልበት መንገድ እያጠና በጠቅላላ ጉባኤው ሲፈቀድ ስራ ላይ ያውላል።

## አንቀጽ 4.5
## ሊቀመንበር

4.5.1 የቦርዱን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ በሊቀ-መንበርነት ይመራል።

4.5.2 የእድሩ ስራ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት እንዲከናወን ከቦርድ አባላት ጋር በመሆን ያቅዳል፣ የእድሩን ስራ ይመራል፣ አባላትን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል።

4.5.3 የቦርድ ስብሰባን ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

4.5.4 የሥራ ክንውን ዘገባ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል።

4.5.5 አስቸኳይ ሁናቴ ካጋጠመ ከቦርዱ ጋር በመመካከር ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል።

4.5.6 የወጭ ማዘዣዎችንና ደብዳቤዎችን በዕድሩ ስም ይፈርማል።

## እንቀጽ 4.6 ምክትል ሊቀመንበር

4.6.1 ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ጊዜ ሊቀመንበሩን ተክቶ ከተራ ቁጥር 4.5.1 እስከ ተራ ቁጥር 4.5.6 ያሉትን ተግባራት ያከናውናል።
4.6.2 የእድሩ አሠራር በሚቀላጠፍበት ሁኔታ ላይ አጠቃላይ ጥናቶችን እያደረገ ለስራ አመራር ቦርድ ያቀርባል።

4.6.3 ስለ ቀብር ቤቶች፣ትራንስፖርት፣ እና ስለመሳሰሉት ከዕድሩ ሥራ ጋር ስለሚገናኙ ተቋማትና አገልግሎቶች አስፈላጊውን ጥናት እና ክንውን ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል።

4.6.4 ዕድሩ ከጋራ ዋስትና ወይም መድሕን ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ አጥንቶ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

4.6.5 የእድሩን ዓላማ ለማስፈጸም ያግዛሉ ተብለው የሚገመቱ ኮሚቴዎችን የማቋቋም ጥረቱን በኃላፊነት ይመራል።

4.6.6 ዕድሩ ሕጋዊ አካል ለማድረግ እና ይህን ይዞ ለመቆየት የሚያስፈልገውን ሁኔታ በመከታተል ስራ ላይ ያውላል።

## አንቀጽ 4.7 ጸሐፊ

4.7.1 የዕድሩን አባላት የስም ዝርዝር ይይዛል።

4.7.2 የስራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ አጀንዳ ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ በየወሩ የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባሎችን ስብሰባ ይጠራል

**4.7.3 የስብሰባዎችን ቃለጉባኤ ይይዛል፣ ያዘጋጃል፣ ለቦርዱ ያቀርባል።**

**4.7.4 የእድሩን ጽህፈት ቤት ሥራ ያከናውናል።**

## አንቀጽ 4.8 ገንዘብ ያዥ

**4.8.1 በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለእድሩ ገቢ ሊሆን የሚገባውን ገንዘብ በየጊዜው እየሰበሰበ በእድሩ የባንክ ሂሳብ ያስቀምጣል።**

**4.8.2 በመመሪያው መሰረት ዕድሩ ለአባሎች የሚሰጠውን ድጋፍ ወይም ክፍያ ቦርዱ ሲወስን ይፈጽማል።**

**4.8.3 ወጪዎቹ በበጀት ከተፈቀደው በላይ አለመሆናቸውን ይከታተላል።**

## አንቀጽ 4.9 የሂሳብ ሹም (አካውንታንት)

**4.9.1 የእድሩን የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።**

**4.9.2 የእድሩን የገቢና የወጪ ደረሰኞች ይይዛል።**

**4.9.3 ገቢዎች በአግባቡ የተሰበሰቡ መሆኑን መርምሮ ያረጋግጣል።**

**4.9.4 የእድሩን ሂሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ያቀርባል።**

**4.9.5 በመንግስት ተቋማት የሚጠየቅ የሂሳብና የታክስ ሪፖርት ያዘጋጃል።**

## አንቀጽ 4.10 የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

4.1**0.1 ማንኛውንም የዕድሩን ጉዳይ በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ለአባላት ያስተላልፋል ወይም መተላለፍን ያረጋግጣል።**

**4.10.2 ከተለያዩ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይመሰርታል።**

**4.10.3 እድሩን ለማስተዋወቅና ለማሳደግ የሚረዱ ጽሁፎችን አያዘጋጀ በየቦታው ይሰራጫል።**

**4.10.4 የእድሩን ዓላማ ሊያግዝ ከሚችሉ ተቋማት ሊገኝ የሚችለውን ጥቅምና እርዳታ እየተከታተል ለቦርዱ ያቀርባል።**

**4.10.5 የእድሩን ዓላማ ለማስፈጸም ከሚያግዙ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት ስለዝርዝር ሥራቸው ለቦርዱ ሪፖርት በማቅረብ ዕድሩ በተሻለ ሁኔታ አገልግሎች የሚያገኝበትን መንገድ ያበጃል።**

**4.10.6 የእድሩን በየነ መረብ (ድህረ-ገጽ) እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን የማቋቋም ፣ የማስተደደሩንና የማሳደጉን ጥረት በኃላፊነት ይመራል።**

**4.10.7 አባላት የዕድሩን ድህረ ገጽ እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በሚገባ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ እያጠና ለቦሩድ በማቅረብ ጥናቶችን ስራ ላይ ያውላል።**

## አንቀጽ 4.11 ኦዲተር

**4.11.1 የእድሩ ቦርድ ከጠቅላላ ጉባኤው ውስጥ ሶስት አባላት ያሉበት ኦዲተሮችን ይሰይማል።**

**4.11.2 የኦዲተሮቹም ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል።**

**4.11.3 ኦዲተሮቹም በሂሳብ ባለሙያው ተዘጋጅቶ የቀረበውን ዓመታዊ ሪፓርት መርምረው የደረሱበትን ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባሉ።**

**4.11.4 ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ኦዲተሮቹ ሙሉውን ዓመት የሚያጠቃልል፣ የወራት፣ የሩብ ዓመት፣ ወይም የግማሽ ዓመታት ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።**

### አንቀጽ 4.12. የንዑስ ኮሚቴ አስተባባሪው ኃላፊነት

4.12.1. የንዑስ ኮሚቴ አስተባባሪው በአንቀጽ 4.4.3 መሠረት የዕድሩን ሥራ ለማቀላጠፍ አስፈላጊ የሆነ(ኑ) ንዑስ ወይም ንዑሳን ኮሚቴ የተመለከተ ጥናት አጥንቶ ለሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ያቀርባል ፣ ሲጸድቅም የሚቋቋሙትን ንዑሳን ኮሚቴ ያስተባብራል።

## ምእራፍ 5 የእድሩ ሕገ-ደንብ

**5.1 ይህ ሕገ-ደንብ የኢትዮጵያውያኖች የመረዳጃ እድር በኔዘርላንድስ ሕገ-ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። ይህ ሕገ ደንብ ከጃንዋሪ 1 ቀን 2023 ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።**

**5.2 የኢትዮጵያውያኖች የመረዳጃ እድር በኔዘርላንድስ አመታዊ የስራ አፈፃፀም እና የሒሳብ አያያዝ በጃኑዋሪ 1 ቀን የሚጀምር ሲሆን የዓመቱ ሒሳብ በዲሴምበር 31 ይዘጋል።**